ደምብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

ተዛማጅነት ያላቸው ሠነዶች፦ ACA፣ ACF፣ ACF-RA፣ IHC-RA፣ IJA-RA፣ IOE-RB፣ ISB-RA፣ JEA-RA፣ JEC-RA፣ JEG-RA፣ JHB-RA፣ JHE-RA

የሚመለከተው ጽ/ቤት፦ Chief of Teaching, Learning, and Schools

እርግዝና ላይ ላሉ እና ልጅ ለሚያሳድጉ ተማሪዎች ትምህርት ስለሚቀጥሉበት ሁኔታ መመሪያ

I. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ነፍሰ ጡር እና የወለዱ እመጫት ተማሪዎችን በተመለከተ የፌዴራል እና የስቴት ህግን ስለማክበር እንደአግባቡ ሀላፊነት መስጠት እና እርጉዝ እና የወለዱ እመጫት ተማሪዎች በትምህርታቸው እንዲቆዩ የመርዳት ሂደትን ይፋ ማድረግ።

II. **ትርጓሜ**

የወላጅነት ኃላፊነት ያለባ(በ)ት ተማሪ ማለት የልጅ እናት፣ አባት ወይም ህጋዊ ሞግዚት የሆነ ተማሪ ማለት ነው።

III. **ቅደም-ተከተል**

A. እርጉዝ ወይም ልጅ የሚያሳድጉ ተማሪዎች ላይ መድልዎን ወይም ጾታዊ ጥቃትን/ትንኮሳን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች

1. የፌደራል ህግ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ ፀረ መድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃትን ማዳበር፣ እና የቦርድ ፖሊሲ ACF፣ ጾታዊ ጥቃት/ትንኮሳ፣ የእርግዝና እና የወላጅነት/ አራስ/እመጫት ሁኔታን ጨምሮ በትምህርታዊ መርሃግብሮች እና እንቅስቃሴዎች ላይ በጾታ ምክንያት የሚደርስባቸውን መድልዎ ወይም ጥቃትን መከልከል።

   a) ትምህርት ቤቶች የተማሪን እርግዝና ወይም የወላጅነት ሁኔታ መሰረት በማድረግ ተማሪን በማንኛውም የትምህርት ክፍል ወይም የትምህርት ፕሮግራም ላይ እንዳይሳተፉ፣የአካል ማጎልመሻ ትምህርት፣ የላቀ ችሎታ ምደባ ወይም የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ትምህርት፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ ፕሮግራሞች፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል የሚካሄዱ ስፖርቶች፣ ሆነር ሶሳይቲስ ወይም የተማሪ አመራር እድሎችን እንዳይሳተፉ ማድረግ አይችሉም።

   b) ት/ቤቶች ከ እርግዝና ወይም ልጅ ከማሳደግ/ወላጅነት ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካላዊ እና ስሜታዊ ሁኔታ ምክንያት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚያደርጉ ከሆነ፣ሌሎች ተማሪዎች እንዳይሳተፉ በሚፈቅዱበት ተመሳሳይ ሁኔታ መፍቀድ ይኖርባቸዋል።

   c) ትምህርት ቤቶች አንድ ነፍሰ ጡር ወይም ወላጅ ተማሪ በክፍል እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ እንድትሳተፍ ለመፍቀድከተማሪዋ የጤና እንክብካቤ ህክምና ባለሙያ የተሰጠ ማስረጃ ሊፈልጉ የሚችሉት ከጤና እንክብካቤ

ህክምና ባለሙያ መቅረብ ያለበት የአካል ወይም ስሜታዊ ሁኔታ ችግር ያለባቸውና ህክምና የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሁሉ የሰነድ ማስረጃ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ብቻ ነው።

d) ለእርጉዝ ተማሪ የትምህርት ፕሮግራም ማመቻቸትን አስመልክቶ፣ አስፈላጊ ሲሆን፣ ት/ቤት በመደበኛው ፕሮግራም ላይ ተገቢ እና የተማሪን የእርግዝና ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት (ለምሳሌ፡- ት/ቤቱ ተለቅ ያለ ዴስክ መስጠት ይኖርበት ይሆናል፣ ወደ መፀዳጃ ክፍል ቶሎ ቶሎ መመላለስ ካስፈለገ መፍቀድ፣ ወይም አሳንሰር/ኤሌቬተር ለመጠቀም ጊዜያዊ ፈቃድ መስጠት) ጊዜያዊ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልጋል።

2. ከት/ቤት ሰራተኞች በተጨማሪ የተማሪ ደህንነት እና ህግ አስከባሪ ክፍል ከእርግዝና ወይም ከወላጅነት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ምክንያት ከሚደርስባቸው መድልዎ ወይም ትንኮሳ ከፆታዊ ትንኮሳ ወይም ተገቢ ካልሆነ የወሲብ ባህሪ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መፍትሔ ለሚፈልጉ ተማሪዎች መመሪያ፣ ድጋፍ እና/ወይም ምክር ይሰጣል።

B. የምክር አገልግሎት/ካውንስሊንግ

1. መምህራን ወይም ሌሎች ሠራተኞች እርጉዝ ወይም ወላጅ ተማሪ መኖሩን ካወቁ ወይም ይሆናል ብለው የሚያምኑበት ምክንያት ካላቸው ለት/ቤት ካውንስለር፣ ለት/ቤት ማህበረሰብ ነርስ (SCHN)፣ ለት/ቤት የጤና ቴክኒሻን፣ ወይም ለርእሰ መምህር/(ተወካይ) ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

2. እርጉዝ ወይም ልጅ አሳዳጊ ወላጅ ተማሪ እርግዝናዉ በምስጢር እንዲያዝ ሠራተኞቹን ከጠየቁ፣ ሠራተኞቹ በምስጢር መጠበቅ አለባቸው።

a) የት/ቤት ካውንስለርን፣ ወይም SCHN አገልግሎቶችን ለመጠቀም እንድትችል ተማሪን ማደፋፈርና መርዳት ያስፈልጋል፣ እናም

b) እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ከትምህርት ቤቱ ካውንስለር እና/ወይም ከርእሰመምህር ጋር በመመካከር መረጃው ሚስጥራዊ ሆኖ እንዲቆይ እና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እንዳይጋራ ለማድረግ የሚጥር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

3. ከሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ IJA-RA ጋር የሚጣጣሙ የት/ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች፣ የት/ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች

a) ተማሪዋ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ተገቢ የማህበራዊ አገልግሎቶች እና የጤና አጠባበቅ ሪሶርሶችን ሁሉ እንድትጠቀም እንዲሁም የሚረዱ ድጋፍ የሚሰጡ ሰዎችን እንድታውቅ ተማሪዋን ማማከር፣

b) ለነፍሰ ጡር ወይም ለወላድ ተማሪዎች በአካዳሚክ፣ በሙያ፣ በጤና፣ በግላዊ ሁኔታ እና የግል እድገት መስኮች ምላሽ መስጠት፣

c) ያሉትን የትምህርት እድሎች ከነፍሰ ጡር ወይም ከወላድ ተማሪ ጋር ማገናዘብ እና ሁለቱንም አማራጮች እና ለማደግ አስፈላጊ ድጋፎችን ማቀንቀን፣ እነዚህም ክሬዲት

ማሻሻልን፣ በግል ማጥናትን፣ ሁለትዮሽ ምዝገባን፣ በትርፍ ሰዓት መማር ወይም የትምህርት እድገታቸውን ለመጠበቅ ሌሎች የትምህርት አማራጮችን መፍቀድ፣ እና

d) የመመረቂያ እቅድን ለማሣካት ከእርጉዝ ወይም ልጅ ከምታሳድግ ወላጅ ተማሪ ጋር መሥራት።

4. በተጨማሪ፣ በእርግዝና ወይም በወሊድ ምክንያት ትምህርት ቤት ላቋረጡ ተማሪዎች ከሌሎቹ ጊዜያዊ የጤና እክል ላላቸው የ MCPS ተማሪዎች እንደሚደረገው በተመሳሳይ መልኩ ጊዜያዊ የማስተማር አገልግሎት ሊሰጣቸው ይችላል።

5. SCHN፣ የትምህርት ቤት የጤና ቴክኒሻን፣ ርዕሰ መምህር/ተወካይ፣ የትምህርት ቤት ካውንስለር እና/ወይም የተማሪ ሰራተኛ፣ እንደአግባቡ ለነፍሰ ጡር ወይም ለወላድ ተማሪ ያሳውቃል/ታሳውቃለች –

a) በፌዴራል ሕግ መሠረት ያሏቸው መብቶች

b) በማህበረሰብ ኤጀንሲዎች እና አጋሮች የሚሰጠውን የማህበራዊ አገልግሎት እና የጤና እንክብካቤ ጭምር ያሉትን ድጋፎች እና ሪሶርሶች ማሳወቅ፣

c) ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተመጣጣኝ እና አስተማማኝ –

(1) የሕፃናት እንክብካቤ እና ቅድመ ትምህርት አገልግሎቶች፣ እና

(2) ወደ ትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ወደ ቤታቸው የመጓጓዣ አገልግሎቶች።

C. የትምህርት ክትትል እና የማሟያ - ሥራ

1. ተማሪ በእርግዝና ወይም በወላጅነት ምክንያት ከት/ቤት መቅረት በፌደራል እና በስቴት ህግ መሠረት በ MCPS ደንብ JEA-RA ላይ እንደተገለጸው ህጋዊ መቅረት ነው። የተማሪ ትምህርት መከታተል

2. ከዚህ በላይ በ II.B ላይ ከተቀመጡት ስልቶች በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ነፍሰ ጡር ወይም ወላጅ ተማሪ ተማሪዋ በሌለችበት ጊዜ ውስጥ ያመለጧትን የትምህርት ስራዎች ቢያንስ ትምህርት ያመለጣትን ቀናት እንድታሟላ መፍቀድ እና ተማሪዋ እንደአስፈላጊነቱ ያመለጣትን ትምህርት ወደምታሟላበት አማራጭ መምራት አለባቸው።

a) ሴሚስተሩን እንደገና መማር

b) በኦንላይን ኮርስ-ክሬዲት ማሟያ ፕሮግራም መሳተፍ

c) ተማሪዋ(ው) በያዘችው/በያዘው እርምጃ እንድትቀጥል/እንዲቀጥል እና ዘግይታ እንድትጨርስ/ዘግይቶ እንዲጨርስ/መፍቀድ።

D. ጡት ማጥባት/ማለብ

1. እያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በት/ቤቱ ውስጥ ጡት የሚያጠቡበት/የሚያልቡበት የግል ቦታ ማዘጋጀት አለበት–

a) ቢያንስ አንድ ዝርግ የሆነ የሚቀመጡበት አማራጭ ቦታ እና በአቅራቢያ የሚገኝ የኤሌትሪክ ሶኬት የጡት ማለቢያ ፓምፕ መሳሪያ ማስቀመጥን ያካትታል፣ እና

b) ይህ ማለት መታጠቢያ ቤት ወይም ቁም ሳጥን አይደለም።

2. ጡታቸውን የሚያልቡ ተማሪዎች በግል ጡት የሚያልቡበት ቅርብ ቦታ ላይ የሚገኝ ማቀዝቀዣ ማግኘት አለባቸው።

E. ትምህርት ማቋረጥ

ተማሪዋ በእርግዝና ወይም በወለደች ጊዜ ለማቋረጥ ከፈለገች፣ የት/ቤት ሰራተኞች ...ለማድረግ ሁሉንም ጥረት – ማድረግ አለባቸው።

1. ተማሪዋ ትምህርት ቤት ከማቋረጧ በፊት የኮርስ መስፈርቶችን እንድታስተካክል መርዳት፣

2. ከተማሪዋ ጋር፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር፣ ለተማሪዋ የጤና አገልግሎት ከሚሰጡ ባለሙያዎች ጋር፣ አቀንቃኞች ጋር፣ አስተማሪዎች፣ ካውንስለሮች፣ የተማሪዎች ሰራተኛ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር እንደአግባቡ ችግር ፈቺ ስብሰባ ማድረግ።

3. የ MCPS ቅጽ 565-4a እንደአግባቡ በመሙላትትምህርታዊ ቃለ መጠይቅ ማድረግ ትምህርት ማቋረጥን መከላከል፣ እና

4. በ MCPS ደንብ JEC-RA ላይ እንደተገለጸው የተማሪ ከክፍል እና ከትምህርት ቤት ማቋረጥ የመከላከል ሰነዶችን እና ተጨማሪ ሂደቶችን መከተል።

F. የሙያ ትምህርት

በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት MCPS በት/ቤት ከላይ የተዘረዘሩትን ሰራተኞች እና ሌሎችንም የሚያቀርብ ሲሆን በዚህ ብቻ አይወሰንም–

1. ስለ ትምህርት ቤት ማጠናቀቅ እና የወደፊት እድሎች ለእርጉዝ እና ወጣት የሚያጠቡ ወላጆች ፍላጎታቸው የተመለከተ ድጋፍ መስጠት፤

2. ስለነፍሰ ጡር እና ወጣት ወላጅ Title IX ጥበቃ መረጃ፣

3. አስተማማኝ፣ የሚደግፍ፣ ምላሽ ሰጭ ባህል ያለው፣ ለሁሉም ተማሪዎች በእኩልነት፣ ተቀባይነት እና ተደራሽነት ላይ ያተኮረ የትምህርት ክፍል ስርዓት መዘርጋት፣ እና

4. ለጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት የተጋለጡ እርጉዝ እና የወለዱ ተማሪዎችን በመለየት እና በመደገፍ የሰራተኞች ግንዛቤን ለመጨመር የሚያገለግሉ ስልቶች።

G. ድንጋጌ

ለነፍሰ ጡር እና ለወላድ ተማሪዎች የተሰጡ ድንጋጌዎች፡-

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መመሪያ ላይ

ተገልጿል፣ እና

2. ለተማሪዎች መግለጫ በሚሰጥ ጊዜ ከተማሪ ጋር ውይይት ማድረግ።

ተዛማጅ ምንጮች: 1972 የትምህርት ማሻሻያ ህግ Title IX፣ እንደተሻሻለው፣ የ ዩ. ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ቢሮ “መብትን ማወቅ፡ እርግዝና ወይም ወላድ/ልጅ ማሳደግ? Title IX በትምህርት ቤት ከሚደርስ መድልዎ ይጠብቅሻ(ሃ)ል" እና "የእርጉዝ እና የወለዱ ተማሪዎችን የአካዳሚክ ስኬት መደገፍ በ 1972 የትምህርት ማሻሻያ Title IX" የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ §7-301.1 እና §4-139; በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ስለ የመብት እና ሀላፊነት የተማሪ መመሪያ

የዚህ ደንብ ታሪክ፦ የቀድሞ ደንብ ቁጥር 335-6 ኤፐሪል 12, 1977፣ ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል፣ ጃኑወሪ 22, 1996 ተሻሽሏል።አክቶበር 26, 2006 ተሻሽሏል፣ ፌብሩወሪ 26, 2018 ተሻሽሏል፣ ሴፐቴምበር 25, 2018 ቴክኒካዊ ማሻሻያ ተደርጓል፣
ኤፐሪል 28, 2022 ተሻሽሏል።